# አሉባልታ እያናፈሱ የጠነከረ ተቃዋሚ ፓርቲ ለመፍጠር ግብዓት መሆን አይቻልም!

(ከሄኖክ ሄደቶ henhed77@yahoo.com)

እውቀት ኃይል ነው (Knowledge is Power) ይባላል። ከእውቀትም በእውነት ላይ የተመሠረተ እውቀት ደግሞ በይበልጥ ኃያል እንደሚሆን ግልፅ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ስሜት ለጊዜው የሚቆይ ወረተኛ ጉልበት እንጂ ዘወትር አቅም የሚፈጥር እምቅ ኃይል ሊሆን አይቻለውም። በተለይማ በውሸት ላይ የተመሠረተ ስሜት ውሎ አድሮ የውሃ ላይ ኩበት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

እንኳን ፖለቲካ፣ አዋጭነቱ አስተማማኝ ነው ተብሎ የታመነ ንግድ እንኳን ኪሳራ እና ውድቀት ሊያጋጥመው ይችላል። ይህ በጭራሽ ሊያስገርመን አይገባም። ቁም ነገሩ ካለፈ ውድቀት ተምሮ ወደ ፊት በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ ያው ስህተት ወይም የስህተቱ መሠረታዊ ምንጭ ጉዳት እንዳያደርስ ከማድረጉ ላይ ነው። ሌላው አስፈላጊ ነገር ከይሉኝታ ተላቆ እራስንም ሆነ ሌሎችን ለመተቸት መድፈር ነው። እነዚህ መሠረታዊ ግብአቶች ባልተሟሉበት ሁናቴ ይቅር ስለሌሎች ስለራስ ያለፈ ታሪክ እንኳን ትክክለኛ ግንዛቤ መያዝ አይቻልም።

በሀገራችን የጠነከረ ተቃዋሚ አለመኖር ሁላችንንም ሊያሳዝነን የሚገባ ጉዳይ ነው። ሆኖም አሁንም ከላይ ከጠቀስናቸው ችግሮች ሳይላቀቁ የችግሩን መሠረታዊ ምንጭ ለማወቅ የሚደረግ ጥረት ችግሩን በይበልጥ ከማወሳሰብ እና እንዳይፈታ ደንቃራ ከመሆን ውጪ መፍትሄ አይሆንም። የዴሞክራሲ ትግል ከአንድ ወቅት የምርጫ ክስተት ባለፈ ጥልቅ እና ውስብስብ ባህሪያት እንዳሉት መገንዘብ ተስኖን ምርጫ 1997'ትን በታሪካችን የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እድል እንደሆነ አድርጎ መመልከት እራስን ለከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ መዳረግ እና የተባለውም የዴሞክራሲ ትግል ክፉኛ እንዲሽነፍ መፍቀድ ማለት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ማየት ከጀመርን ሁለት አስርት ዓመታት የሞላን ቢሆንም፣ በዚህ አጭር በማይባል ጊዜ ውስጥ ለምን ጠንካራ ተቃዋሚ መፍጠር እንዳልቻልን አንድ ጊዜ ሳይሆን ደጋግመን ልንወያይበት የሚገባ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ከምር ተነጋግረን አንድ የሚያስማማ አስተሳሰብ ላይ መድረስ ከቻልን የተባለውን ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ ለመፍጠር ከግማሽ መንገድ በላይ ሄድን ማለት ይሆን ነበር። ከዚህ በተለየ ጉዳዩ በተነሳ ቁጥር፣ "በ1997ቱ ምርጫ ቅንጅት የሚባል ስብስብ ተፈጥሮ ነበር ምን ያደርጋል ልደቱ አፈረሰው" የምትል አንድ ሀረግ እያቀረቡ ቁንፅል መከራከሪያ ማቅረብ እንኳን ሌሎችን እራስንም በጥቂቱ ማሳመን አይቻልም።

ከአንድ ሣምንት በፊት ባነበብነው የሪፖርተር ጋዜጣ እትም ላይ "እኔ የምለው" በሚል አምድ ፅሑፍ "ያበረከቱልን" እና በቀድሞው ቅንጅት ውስጥ እሳተፍ ነበር ሆኖም አሁን የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ስላልሆነ፣ ነፃ ምርጫን ለማስፈፀም የሚያስችል ሥርዓት ስላልተዘረጋ፣ ፍርድ ቤቶች ነፃ ስላልሆኑ፣... በአጠቃላይ በሰሞነኛው ቋንቋ "የፖለቲካ ምህዳሩ ስለጠበበ" ከፖለቲካ ተሳትፎ እራሳቸውን ማግለላቸውን የሚገልፅ አስቂኝ ማብራሪያ ያቀረቡልን ሰው፣ ለቅንጅቱ መበታተን ምክንያት ናቸው ያሏቸውን አቶ ልደቱን "ቅንጅት ውስጥ አልገባም ብለው ፕ/ር መስፍን ለምነው አስገቧቸው" ይሉና ትንሽ ወረድ ብለው ደግሞ "አቶ ልደቱ ቅንጅቱን የመበታተን ልዩ ተልእኮ ይዘው ገቡ" የሚል እርስ በርስ የሚጣረስ አስተያየት አቅርበዋል።

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ልዩ ተልእኮ ያለው ሰው አፈርሰዋለው ብሎ ወዳሰበው ስብስብ ለምኖ እና ተሹለኩልኮ ይገባል እንጂ ተለምኖ እና ታላቅ ክብር ተሰጥቶት አይገባም። ፅሑፉን የፃፉልንም ሰው ከሁለቱ ሀሳቦች አንዱን መርጠው እርሱን በደንብ ቢያብራሩልን ይሻላቸው ነበር። ለነገሩ ፀሐፊው የተለያዩ ሃሳቦችን በአንድ ላይ ለማቅረብ ሲሞክሩ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ አይቼባቸዋለሁ።

'ዛሬ በኢትየጵያ ጠንካራ ተቃዋሚ አለ' ብሎ መከራከር ሌላ፣ 'የቀድሞው ቅንጅት ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ጠንካራ የሚባል ተቃዋሚ ሊፈጠር አይችልም' ብሎ ማለት ሌላ። 'ወጣቶች ምንም ያልተበረዘ አእምሮ ስላላቸው ኃሳብን በንፁህ ህሊና ለመመዘን ይችላሉ' ብሎ ማብራራት ሌላ፤ 'ወጣቶች አእምሮአቸውን ክፍት አድርገው ማድመጣቸው ያጠራጥረኛል' ብሎ ማለት ሌላ። 'እንደ አቶ ኃይሉ ሻውል ያለ መሪ መቆየት አለበት። ማደራጀቱን፣ መታገሱን እና ሰው ማድመጡን ያውቅበታል' ብሎ ማሞጋገስ ሌላ፣ 'አቶ ሃይሉ ምክር ያሻቸዋል አለበለዚያ ወዳጅ ዘመድ እንዳይከተላቸው መምከር ይኖርብናል' ብሎ ትችት ማቅረብ ሌላ።

እንደዚህ ዓይነት እርስ በርሱ የሚጋጭ ሀሳብ በአንድ አእምሮ ውስጥ ለማጨቅ መሞከር የህሊናን ኃሳብን መዝኖ እና ትክክለኛውን መርጦ የመያዝ መብት መጋፋት እና ከ"ማሰቢያ ማሽንነት" ወደ "ኃሳብ ማጠራቀሚያ ጎተራነት" እንዲቀየር መሞከር ይሆናል። ይህ ተይዞ ደግሞ እንኳን ለሀገር እና ለሕዝብ የሚጠቅም ፖለቲከኛ ሊኮን የራስንም ማኅበራዊ እና የስራ ሕይወት በአግባቡ መምራት አይቻልም።

እንደዚህ ዓይነት በጥቂቱ እንኳን ያልጠራ አስተሳሰብ ተይዞ ስለምን ጠንካራ ተቃዋሚ በሀገሪቱ ሊፈጠር እንዳልቻለ ሚዛናዊ አስተያየት ማቅረብ ከቶም አይቻልም። ትንሽ እንኳን ሚዛን የሚደፋ ፅሁፍ መፃፍ ሲያቅት የአቶ ልደቱንና የኢዴፓን ስም እዚህም እዚያም እንደማጣፈጫ ቅመም ጣል ማድረግ ለማንም እንዳልበጀ መገንዘብ ጥሩ ነው።

የፓርቲ ጥንካሬ የሚመነጨው አንድም ከሚመራበት አጠቃላይ አስተሳሰብ እና ከአመራሩ የማሰብ እና የመወሰን ነፃነት እንደሆነ ግልፅ ነው። በፖለቲካ ተሳትፎው የፖለቲካ መሪዎችን እየወለደ "ጎሽ እደግ ተመንደግ" ከማለት ይልቅ ትንሽ ሲያድጉ አናት አናታቸውን የሚል ወይም እንዲባሉ የሚፈቅድ ኅብረተሰብ የተመሰከረለት ብሔራዊ አጀንዳ ቢኖረው እንኳን ለድል ሊበቃ አይችልም። የፖለቲካ መሪዎች በሂደት በደረሱበት የአስተሳሰብ ደረጃ አንዳንድ ጊዜ ከሕዝብ አስተያየት (Public Opinion) በተቃራኒ በመቆም ለሕዝብ ጥቅም (Public Interest) መከበር ሲሉ ስሜት ሊጎዳ የሚችል እና ለጊዜውም ቢሆን የፖለቲካ ድጋፍን የሚያዳክም አቋም የመውሰድ አስገዳጅ አጣብቂኝ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ይጠበቃል።

የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና አቶ ልደቱም ብዙ የለፉለት፣ የታሰሩለት እና መከራ ያዩለት የዴሞክራሲ ትግል የመውደቅ እና ያለመቀጠል አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት ሰዓት የወሰዱትን ከቅንጅት የመነጠልና ፓርላማ የመግባት ውሳኔ በጥሞና ከመመርመር ይልቅ ለሞራልም ሆነ ለይሉኝታ ቦታ በማይሰጥ ዘለፋ ለማኮሰስ መሞከር ጠንካራ ተቃዋሚ እንዳይፈጠር አንድ ደንቃራ ከመሆን የተለየ ሌላ ገንቢ ዜጋ አያደርግም። በአቶ ልደቱም ላይ የደረሰው ታሪክ በመጥፎነቱ የሚያስታውሰው ድርጊት በዚሁ ተቋጭቶ ወደ አእምሯችን ካልተመለስን እና ስሜታዊነት ለምክንያታዊነት ቦታ እንዲለቅ ቁርጥ ውሳኔ ካላደረግን እንደምን ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ሊፈጠር እንደሚችል ለእኔ ጨርሶ ግልፅ አይደለም። በዚህ መንገድ የፖለቲካ መሪዎች በጊዜያዊ የዕወደድ ባይነት ፖለቲካ ተሸብበው ትግሉን እንዲመሩ በማስገደድም እንዴት ለድል ልንበቃ እንደምንችል ግራ የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ ዓይነቱን በአድሏዊነት እና በይሉኝታ ቢስነት የተሞላ የፖለቲካ ሜዳ የተመለከቱ ዜጎችስ ምን ፍለጋ ተቃዋሚዎችን እየተቀላቀሉ ለጠንካራ ፓርቲ መፈጠር ወሳኝ ድርሻ ሊወጡ እንደሚችሉ በፍፁም አይታየኝም።

ሰው ያለስሙ ስም ሲለጠፍበት የማይጠየፍ፣ የፖለቲካ መሪ ጥቅሙ እና ጉዳቱ በውል ያልተፈተሸ የተለየ የፖለቲካ አቋም በመያዙ ብቻ ቤተመቅደስ እንደገባች ውሻ የሚያራክስ፣ በሚያራምደው የፖለቲካ አቋም አንድ ሰሞን "ማንዴላ" ብሎ አንቆለጳጵሶ በሣምንቱ "ከሀዲ" ብሎ የሚሳደብ፣ ለሁለንተናዊ ድል ለመብቃት መሪ እንዲሆኑ ድጋፉን የሰጣቸውን ሰዎች በአንድ ሚሊዮን ብር መኪና ወይም ሸራተን ሆቴል ባለ አልጋ አንሶላ ይደለላሉ ብሎ የሚጠራጠር፣ በአጠቃላይ በሰሞንኛ የሕዝብ ጠላቶች አሉባልታ የሚታለል እና የሚነዳ ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ በጭራሽ ለጠንካራ ተቃዋሚ መፈጠር ግብአት አይሆንም! ህሊናን ለምክንያታዊነት ዝግ በማድረግ እና ደመ ነፍሳዊ የአድማ አቋም በመያዝ ከቶም ሁሉን አቀፍ የስርአት ለውጥ ማሳካት አይቻልም!